# ober 6, 2010

## «የአበባ ወር» ወርኀ ጽጌ



(ማ/ቅዱሳን ድረ ገጽ):- በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከመስከረም 26 ቀን እስከ ኅዳር 6 ቀን ያለው ጊዜ ወርኀ ጽጌ ይባላል። ይህ ወቅት ምድር በአበቦች ቀለምና መዓዛ የምታጌጥበት በመሆኑ «የአበባ ወር» ወርኀ ጽጌ ተብሏል።

አበባ የፍሬ እናት ነው። አበባን ያየ ሰው ሕይወቱ በተስፋ ትሞላለች። መልካሙ ፍሬ ከአበባው ይገኛልና። እመቤታችንም የተባረከ ፍሬ መድኃኒተ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን ያስገኘች አማናዊቷ አበባ ናት። የአዳም ተስፋ መፈጸሙን፣ የነቢያት ትንቢት መድረሱን ያበሰረችን የድኅነት ምልክት እርሷ ናት። «ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል» እንዳለ ነቢየ ልዑል ኢሳይያስ (ኢሳ 7÷14)።
የአበቦች መፍካት የጥጋብ ዘመን መምጣጡን ያበስራል። ወርኃ ክረምት ዘር ገና በምድር ላይ ስለሆነ ኀተራው ይሟጠጣል። መሶቡ ድንግጥ ይላል። የክረምቱ ጊዜ በጎመንና በቅጠላ ቅጠሉ በጥራጥሬው ጭምር ይወጣል። ከአዲሱ ዘመን መባቻ ጀምሮ ግን «የጎመን ምንቸት ውጣ የገንፎ ምንቸት ግባ» በሚለው ባሕላዊ አገላለጽ የአዲስ እህል ሽታ ይሰማል። የእሸት ጊዜ ይታያል። ይህ ጊዜ ምድር በሥነ ጽጌያት ( በአበቦች ኅብር) አጊጣ፣ ሰማይ በከዋክብት አሸብርቆ የሚታይበት፣ የጠራ ውኃ ከወንዞችና ጅረቶች የሚፈስበት፣ ንፁሕ አየር የሚነፍስበት፣ አዕዋፍ ከተሰደዱበት እየተመለሱ የሚዘምሩበት፣ እንስሳትና አራዊት ለምለሙን ሳር እየነጩ ጥሩውን ወሃ እየተጎነጩ የሚፈነድቁበት ጊዜ ስለሆነ ለፍጥረት ደስ ይላል (መኃልይ 2÷13)።

«የዘንድሮን ክረምት ወጣናት በመላ
አንድ ቀን ሰናድር አንድ ቀን ስንበላ
እኛስ ይችን ክረምት ወጣናት በመላ
በኩርማን እንጀራ ጎመን ተጠቅልላ»

እንደሚባለው ክረምት ያለችውን አብቃቅቶ የሚከረምበት ጊዜ ነው። አበቦች በጋራ በሸንተሩ ሲፈነዱ ማሳውና ጓሮው ሲያብብ ግን የጥጋቡ የእህሉ ወቅት መምጣቱን ይናገራሉ።

የድኅነት ምግብ የጽድቅ ውኃ አጥቶ በሲዖል በረሃ በጽድቅ ረሃብ ለተንገላታው የአዳም ዘር ነፍስ በእግዚአብሔር ቸርነት በጌታችን ሥጋና ደም በጸጋ መንፈስ ቅዱስ የምትጠግብበት ዘመን መድረሱን ያበሠረችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት። ዛሬም ቢሆን የተስፋ መቁረጥና የጭንቀት፣ የደዌ ሥጋና የደዌ ነፍስ ረሃብ ለወደቀባቸው እመቤታችን የመዳን ተስፋቸው ናት። በዚህም የተነሳ ቅዱሳን አበው እመቤታችንን በአበባ መስለው ምስጢር ከምሳሌ በማስተባበር ስደቷን በወርኃ ጽጌ ያስቡታል፡

ይህ የእመቤታችን መታሰቢያ ወር በቤተክርስቲያናችን የሚከበረው በሚከተለው ሁኔታ ነው።

1 ኛ. በማኅሌት
2 ኛ. በቅዳሴ
3 ኛ. በዝክር

ማኅሌት

ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት፣ በአምላካችን ቤት በአደባባዮች የምትቆሙ እናንተ የእግዚአብሔር ባርያዎች ሁላችሁ በሌሊት እጃችሁን አንሱ፣ እግዚአብሔርንም ባርኩ (መዝ 133÷1-2) በማለት እንደተናገረው አባቶቻችን ከቅዳሜ ማታ እስከ እሑድ ጠዋት እንዲሁም በክብረ በዓላት እጆቻቸውን ለጭብጨባና ለሽብሸባ አንስተው፣ በከበሮና በጸናጽል እየወረቡ፣ በመቋሚያ እየዘመሙ፣ ያለ ድካምና መሰልቸት ሲዘምሩ ያድራሉ። ምዕመናንም እንቅልፍ ሳያታልላቸው፣ ድካም ሳይበግራቸው ከአባቶቻቸው ጋር በቤተክርስቲያን በመገኘት በዕልልታ በዝማሬ እያጀቡ ያድራሉ። በዚህ ወቅት የሚቀርበው ዝማሬ ሦስት ወገን ነው።

1. ከቅዱስ ያሬድ ድጓ

ቤተክርስቲያናችንን በዓለም አቀፍ ደረጃ ካሳወቋት ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን መካከል አንዱና ዋነኛው ቅዱስ ያሬድ ነው። የቅዱስ ያሬድ ዜማ ከአርያም የተገኘ በመሆኑ ጊዜ የማይሽረው ዘመን የማይለውጠው የቅድስት ቤተክርስቲያን አንጡራ ሀብት ነው።



ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ዓመቱን ክረምት፣ መጸው፣ ሐጋይ ፀደይ ብሎ በመከፋፈል በየዘመኑ የሚዘመረውን መዝሙር አዘጋጅቷል። በወርኃ ጽጌም ቅዱስ ያሬድ የምድሪቱን በአበባ መሸለም፣ በቡቃያ ማማር፣ የክረምቱን የጭቃና የድጥ ወቅት ማለፍ በተመለከተ እግዚአብሔርን ካመሰገነበት ድርሰቱ እየተውጣጣ ይዘመራል። በተለይ በወርኀ ጽጌ።

2. ማኅሌተ ጽጌ

ይህ መዝሙር የእመቤታችንን ታሪክ ከጽንሰቷ እስከ ልደቷ፣ ክብሯን፣ ንጽህናዋን፣ በሄሮድስ ምክንያት የደረሰባትን ስደትና መከራ የበረሀውን ጉዞ እያነሳ የሚያመሰግን ታሪካዊ ይዘት ያለው ድርሰት ነው።

ማኅሌተ ጽጌን የደረሱት አባ ጽጌ ብርሃን የተባሉ ሊቅ መሆናቸው ይነገረል። ዘመኑም በ 14 ኛው ክፍለ ዘመን ነው። አቡነ ዜና ማርቆስ የምሁርን ሕዝብ አስተምረው ወደ ይፋት በማምራት ወንጌልን በመስበክ ላይ እያሉ «ክርስቶስ ተወለደ፣ ሞተ፣ ተነሣ እያሉ እንዴት ያስተምራሉ;» በማለት አንድ አይሁዳዊ ሊቅ ጠየቃቸው። እርሳቸውም በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 11 ቁጥር አንድ ላይ የጻፈውን የነቢዩን ቃል («ከእሴይ ግንድ በትር ይወጣል፣ ከሥሩም ቁጥቋጦ ያፈራል» የሚለውን) ጠቅሰው ስላብራሩለት በትምህርታቸው አምኖ ተጠምቆ ለመመንኮስ በቅቷል። ስሙንም ጽጌ

ብርሃን በማለት ሰይመውታል።

አባ ጽጌ ብርሃን ምሁረ ኦሪት ስለነበረ አብሯቸው እየተዘዋወረ ሀዲስን ከብሉይ አስማምቶ ከተማረ በኋላ እንደ መዝሙረ ዳዊት 150 አድርጎ ማኅሌተ ጽጌን ከአማካሪው ከወረ ኢለጎው ተወላጅ ከአባ ገብረማርያም ዘደብረ ሐንታ ጋር በመሆን አዘጋጀው። ድርሰቱም ቤት እየመታ በአምስት በአምስት ስንኝ እየተከፈለ ነው።

በዚህ ጊዜም ጾም የጌታንና የእመቤታችንን ስደትና መንገላታት በማሰብ ስለ ፍቅራቸው ባሕታውያን፣ መነኮሳትና አንዳንድ ምዕመናን በፈቃዳቸው ይጾማሉ።

3. ሰቆቃወ ድንግል

«ሰቆቃ» ማለት ለቅሶ ዋይታ ማለት ነው። እመቤታች «ልጄን ይገድሉብኛል ብላ የሄሮድስ ወታደሮች ሲከተሏት፣ የዮሴፍ ልጅ ዮሳዕ የቤተልሔምን ሕጻናት እልቂት ሲነግራት፣ ጥጦስና ዳክርስ የተባሉ ከግብጽ ወደ እስራኤል በሚወስደው መንገድ በጋዛ በር የሚዘርፉ ሽፍቶች ሲያጋጥሟት ያለቀሰችውንና በተወደደ ልጇ ላይ የወረደውን መሪር እንባ በማስታወስ የሚዘመር ነው። ይህም መዝሙር በ 15 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በደብረ ወርቅ ቤተክርስቲያን የድጓ መምህር በነበሩት በመምህር አርከ ሥሉስ እንደተደረሰ ይነገራል።
ወስብሐት ለእግዚአብሔር
http://mahiberekidusan.org/Default.aspx?tabid=88&ctl=Detail